# <u>ለወያኔማ ሞት ሲያንሰው ነው!</u>

በተደጋጋሚ ጉድ ከሚሰማበት አሜሪካ ሰሞኑን የደረሰን ዜና ሞት ለወያኔ መባል የለበትም
የሚሉ ተቃዋሚዎች ብቅ ማለታቸውን ያመለክታል። ፈረንጆች ሲተርቱ እያንዳንዱ ሕዝብ
የሚበጀውን መንግሥት ያዝለታል ይላሉ። ሕዝብ ጨቋኞች ሲመጡበት ለእኔ አትሆኑም
አትመቹኝም ብሎ አሽቀንጥሮ መጣል ማስወገድ ይጠበቅበታል። ዝም ብሎ ከተገዛ ግን
የመጠባት በጅቶታል ተመችቶታልም ብሎ ቢወሰድ ጥፋቱ የራሱ ይሆናል ማለት ነው።

ወያኔ ስልጣን ከያዘ ጊዜ ጀምሮ በፖለቲካው መድረክ ላይ የፖለቲካ ንቃታቸው፤ እውቀታቸ
ውና ብስለታቸው አጠያያቂ ቢሆንም ከእኛ በላይ አዋቂ ለአሳር ብለው አንዳንዶች ስለተሰየ
ሙ የሕዝብ ትግል ሲደናገርና ሲጠቃ ቆይቷል። ወያኔም በሆዱ የሚገዛውን ገዝቶ በማሰማራ
ት ትግልን ሲያደናቅፍና የበሰሉና የነቁትን፤ በእርግጥም ፀረ ወያኔ የሆኑትንም እያፈነና እየገ
ደለ የስልጣን ዕድሜውን አራዝሟል። ገና ከጥዋቱ ወያኔን ልጆቼ፤ አቤት ሲያሳዝኑ ብለው
ትንሽ እባብ ከቶም እባብ አይደለም ሊሉ የተነሱ ጥቂቶች አልነበሩም። ወያኔ የነቁትንና
የነቁበትን ሲገድልና ሲያስር፤ ደብዛ ሲያጠፋና በየዝዋይ--ዴዴሳና ትግራይ ሲያጉር ዝምታ
ወርቅ ነው ያሉም ብዙ ነበሩ። አስመሳዮች ሲንጫጩና ሀቀኞቹ ሲታፈኑ ስናይም ዓመታት
አልፈዋል። ጠላት ወዳጅ ወይም የማይደፈሩ ተብሎ ሲፈረጅና ቡከኑና አስመሳዩ ወይም
የወያኔ ቅጥረኛው ጀግና ተበሎ ሲወደስም ቆይቷል። በተደጋጋሚ ዝብርቅርቅ ፖሊተካ ያልነ
ው ሁኔታ ሰፍኖ ነበር ማለት ይቻላል።

ከሁሉም የጎዳን ግን የወያኔን ማንነትና ምንነነት አለማወቅና ምን ዓይነት ትግል የሚለውንም
ለመረዳት አለመቻላችን ነው። ወያኔ ወዳጅና ኢትዮጵያንም የሚያከብር ነው ብሎ የተሞኙ
ት ለመንቃት ብዙ ጊዜም አልወሰደባቸውም። የዓለም ሀገሮችን ሁሉ ኤርትራን ትገንጠል
ባይ ነኝና ተቀበሉኝ ብሎ ሲማጠን ያደመጠው ሁሉ እግዚኦ አለ ። ሰላምና መረጋጋት ሰፈነ
ያሉትም ደም ማፍሰስ የወያኔ ጌጡ መሆኑን ወዲያውኑ መረዳት ተገደዱ ። አፈናው ሁሉን
በተራ ተራ ጎበኘው። ሀገርም በጠራራ ፀሐይ ስትዘረፍ፤ ንብረቷና ቅርሷ ወደ መለስ ዜናዊ
የትውልድ ቦታ ሲጋዝ ያየ ዜጋ ሁሉ የመጣብን ጭራቅ የሾለ ጥርስ ያለው ሰው በላ አገዛዝ
መሆኑን ማወቅ የግድ ሆነበት። እነ ፕሮፌሰረ አስራት ታሰሩ፤ አደባባይ ኢየሱሰ ዕልቂት ተካ
ሄደ፤ ወተር አንዋር መስጊድ፤ ምስራቅ ወለጋ አርባጉጉም የጭፍጨፋ ቦታዎች ሆኑ፤ ከወያኔ
የተጠጉትም በበኩላቸው እነ አርባ ጉጉን ወለዱ። የወያኔ ወዳጅ ሻዕቢያም በኢትዮጵያ ምድ
ር በዜጎቹ ላይ የበቀልና የግድያ እርምጃ እንዲወስድ ተፈቀደለት--አፈናም አካሄደ ። በርካ
ታ የኢሕአፓ አባላትና የቀድሞው አገዛዝ መኮንኖችም ተይዘው ደብዛቸው ጠፋ ። ጠላት
በተባለው የአማራ ሕዝብም ላይ አሰቃቂ ግፍ ተፈፀመ --ውሎ አድሮ ይህ ግፍ ሌሎችንም

ከጋምቤላ እስከ ኦጋዴን ድረስ ጎብኝቷል።ግጭቶችንም በጎሳ/ብሄረሰብና በሀይማኖት ደረጃ ወያኔ ቀሰቅሶ በሀገር ሁሉ አዳረሰ ። ሀገሪቷም ለወያኔና አረብ ዘራፊዎች በገፍ ተሰጠች፤ ተበዘበዘች ። ዛሬ ሳይሆን ያኔ ወያኔ ስልጣን በያዘ ማዕግስትም ቢሆን የዚህ አገዛዝ ፀረ ኢትዮ ጵያነት ግልፅ ነበር። ዛሬ ሳይሆን ያኔ ከመጀመሪያው የወያኔና ቅጥረኞቹ ሕዝብ ጦርነት ሰልችቶታል ጫጫታ ማደናገሪያና መደረግ የነበረበትን ሁለ ገብ ትግል በአጭሩ መቅጫ መሆኑ ግልፅ ነበር። ዓይን ያለው ይይ ጆሮ ያለው ይስማን ምክር አልቀበል ባዮቹ በዙና፤ የፖለቲካ መድረኩን አጨናነቁና ወያኔ እነሆ 20 ዓመት ሙሉ ሊጫወትብን ቻለ ።

በ1997 የነበረው የሀገር ወዳድ ሀይሎች ህብረት በሰርጎ ገቦችና የባዕድ ቅጥረኞች ባይጠቃ ኖሮ የወያኔ ዕድሜ በዚያው ያከትም ነበር። እንዱ ከሀዲ ወይም አቶ ክህደቱ የተሰጠውን የሻጥር ስራ በወሳኝ ወቅት አካሄደ ። ሁለት የተቃዋሚ መሪ ተብዬዎች ደግሞ ታሪካዊውን የሙት ከተማ አድማ ከአሜሪካና እንግሊዝ ኤምባሲ ተጠሪዎች ጋር ሆነው አከሸፉ ። ህብረ ትም ቅንጅትም የሚሽምደበዱበት ሁኔታ ተረጋገጠ ። ከእስርም በኋላ አስታራቂ ሽማግሌዎ ች በሚል ለወያኔና ለባዕድ ታደሩ ማደሪያዎች ተሰለፉ። ውጤቱን ዜጎች ሁለ ያውቁታል፤ አፍረውበታልም። ወያኔም ብልጥ ነውና ገለባዎችን ጀግና አስመስሎ የዋሆች መሪዎቻችን ብለው እንዲቀበሏቸው አድርጓል። ዛሬ አርአያ ጀግና እየተባሉ በዚህም በዚያም የሚደነቁት ን ስናይ ምን ያህል ወያኔ በፈለገው እንደቃኘንና እንደጎዳን ማወቅ እንችላለን። ወያኔ የሀገር ና የ'ሕዝብ ጠላት ሆኖ እየተገኘ በዚህ ላይ ውዠንብርን መያዝ የመረጡ ክፍሎች ዛሬም መኖራቸው አነጋጋሪ መሆኑ ተገቢ ነው። ወያኔን ጠላት አትበሉ፤ ሞት ለወያኔ አትበሉ የሚሉ ዜጎች ዛሬም አሉ። ምክንያታቸው አነጋጋሪ ነው። ወያኔ እንዳይሞት ፈልገው? እንዳ ይወድቅ? ከወያኔ ለመደራደር? ለመተቃቃፍ? አነጋጋሪ ነው። ሌሎች ለወያኔ ሊያድሩ የቋመጡ ክፍሎች ወያኔን ወያኔ አትበሉት ኢሕአዴግ እንጂ ብለው ሲጮሁ እንደነበር አንረ ሳም። የውድቀት ዳር ዳሩ ከጠላት ለመሞዳሞድ መሞከር መሆኑን እናውቃለን። ጠላትን ወዳጅ ለማለት መገባበዝ ደግሞ የባሰ ነው። ሞት ለወያኔ አትበሉ አቅዋም በመሰረቱ ሕዝባዊ ሳይሆን ወያኔያዊ ነው። ለጠላትም ፍቅር የሚሰብኩ ስለ ፍቅር ዕይታቸው የተዛባ ነው። ፍቅር ስንል ለሕዝብና ለሀገር ነው እንጂ ወያኔ ዓይነቶቹን ሊጠቀልል አይችልም። ለጠላትማ ሞትና ይውደም ተገቢ መፈክሮች ናቸው። ሞት ለወያኔ!

ዛሬ የመለስ አገዛዝ ወደ መቃብሩ እየተጓዘ ነው። ምትኑና ጥቃቱ ሊበዛበት ይገባል እንጂ አታውግዙት አታጥቁት ማለት ስህተት ነው። በፖለቲካው መድረክ ኡኡታ እያበዙ ያሉት ጥራዝ ነጠቆችን ጥግ ማስያዝ ያስፈልጋል። በማያወቁት የሚቀበጣጥሩትን ትዕግስትም ጆሮም መለገስ አያሻም። መስመርን ጎራን መለየት ለሀገራዊ ትግል ስኬት አስፈላጊ ነው።

መስመራቸውና አቅዋማቸው ከወያኔና ባዕዳን ጋር የሆኑትን በጊዜ ማጋለጥና ወግዱ ማለት ለሕዝባዊ ትግል ድል ያስፈልጋል፡፡ ሕዝብ ወይም ዜጋ ነቃ ብሎ ፈሪሳውያኑን ከመድረክ ካራቀ ፤ የሕዝብ መሪዎች ለመሆን የሚወራጩ ቡከኖችን ወግዱ ካለና በሀቅ ለሀገር የሚታገ ሉትን ካከበረ መንገዱ ቀና ሊሆን ይችላል፡፡ አወቅን ባይ ግን ከተመክሮም ቅንጣት ያልተማሩትንም አደብ ግዙ ማለት ያሻል፡፡ ዜጎች ማነው ጠላትና ወዳጅ የሚለውን ዛሬም ካላወቁ መከራችን የሚቆይ ይሆናል፡፡ ሞት ለወያኔ አትበሉ ካሉማ ነገር ተበላሻሽቷል ማለት ነው ፡፡ ለዚህም ነው አርአያ ጀግና ሁሉ ለብዙዎች የተምታታ ጉዳይ የሆነባቸው ፡፡ ወራዳ ከሀዲ ማንዴላ አልተባለም? ወር ሲታሰር ማረኝ ወያኔ የሚለው ጀግና መሪ አልተባለም? የሕዝብ ወገን እየተባሉ የተወደሱ ዘፋኞች ዛሬ የወያኔ ከርሳም አሽከሮች ሆነዋል፡፡አሳዛኝ ክስተት ነው፡፡ ይህን ሁኔታ መቀየር መቻል ያሻል፡፡ ሞት ለወያኔ እንደገና! ለወያኔ ወድቀት ና ውድመት በጋራ እንታገል!!!